**Association of Ethiopians in Europe**

**የኢትዮጵያዉያን ማህበር በአዉሮፓ**

**www.ethiodiaspora.net**

**25.11.2021 (እንደ አዉሮፓ አቆጣጠር)**

# ወቅታዊውን የሀገራችንን ተጨባጭ ሁኔታን በተመለከተ የኢትዮጵያውያን ማህበር በአውሮፓ የአቋም መግለጫ::

## መግቢያ

ማህበሩ በአሁኑ ወቅት : አገራችን ኢትዮጵያ: የተዘፈቀችበትን :የህልውና አደጋ መንስዔውን :መርምሮ : መንስዔውም : ከሥሩ እንዲመክን: የበኩሉን አስተዋፅኦ ለማድረግ ያመቸው ዘንድ ፣ የአደጋውን ምንጭ ነቅሶ በማውጣት ፣ ሕዝባችንና አገራችንን መታደግ ግዴታችን መሆኑን አጥብቆ ያምናል።አገራችን ያለችበትን ባለ ብዙ ፍርጃና : ውስብስብ የህልውና ፈተናዋቿንም: ይገነዘባል።

## ዋነኛ ጠላቶቿን በተመለከተ፣

ዛሬ እናት ሀገራችን ኢትዮጵያ እጅግ ውስብስብ መከራ ውስጥ ተደፍቃ ልጆቿ በግፍ ሕይወታቸውን፣ የሚገብሩባት ሰብዕ : ሰውነታቸው በማንነታቸው: ምክንያት(ማህበራዊ መሠረታቸውና እምነታቸው  ተለይቶ) አማራንና፣ ኦርቶዶክስ ናችሁ ተብለው የዘር ማጥፋት (የዘር ማፅዳት)ወንጀል  ይፈፀምባቸው ከጀመረ እነሆ ከ30 ዓመታት በላይ አስቆጥሯል። በዘግናኝነቱ ወንጀሉም ተጠናክሮ ቀጥሏል። ለጥፋቱም መፍትሔ ካለመገኘቱም : በላይ አፈፃፀሙ፣ በአንድ በኩል በብልፅግና መንግስት ፣  በህወሓትና:  በኦነግ : የተቀናጀ : መዋቅራዊ አሠራር ዘመቻው ተጠናክሮ  በመቀጠሉ ፣ አገር እርስበርስ : በግልፅ የሲቪል ጦርነት ውስጥ ገብታ ሰላምና የዜጎቿ ደህንነት: ከአገሪቱ ርቋል። የዜጎችን በአገራቸው ሠርተው የመኖር መብትና ዋስትና ተገፏል ። የዜጎቿ መታረድ : መገደል ከይዞታቸው  በግፍ መፈናቀል ሀብት ንብረታቸውን : የማውደሙ ሥራ ተጠናክሮ የጥላቻው ጥግ  የሰው ሥጋ እሚበላበት ደረጃ ደርሷል ።

ይህንን በአግባቡ መከላከልና በአገሪቱ ሠላምና:  ፀጥታን  የማስፈኑ ኃላፊነት የመንግስት ሆኖ ሳለ፣  የብልፅግና መንግስት  የአመራር: ንዝህላልነት፣ (ብቃት ማጣት: አልያም በሌሎች ህቡዕ ድርጊቶች) ምክንያት መከወን ባለመቻሉ አገር በሁለንተናዊ :  በፓለቲካ  የኢኮኖሚና : የማህበራዊ ሕይወት  ቀውስና  ውድቀት ውስጥ ተንኮታኩታ ተዘፍቃለች።

ከዚህም የተነሳ ከአንድ ዓመት በላይ የቀጠለው ዘመቻ፣  ወደለየለት ጦርነት ተሸጋግሮ በዚህም አጋጣሚውን ተጠቅመው  የውጭ ኃይሎች በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ እንዲገቡና  የኃላ ተፅእኖ በማሳደር ሚናቸውን እንዲጫወቱ አመቺ ሁኔታ ተፈጥሮላቸዋል። ይህንንም ለራሳቸው ዓላማ እንደ ግብአት በመውሰድ ኃያላን ኃይሎች ፣ ለህወሓት ወረራ በማድላት ግልፅ አቋማቸውን ፣ በአመዛኙ ይፋ አድርገዋል።  እነዚህ የመሳሰሉትን ነባራዊ  ሁኔታዎች፣  ከግንዛቤ ፣ በማስገባት የኢትዮጵያውያን ማህበር  በአውሮፓ የሚከተለውን የአቋም መግለጫ አውጥቷል።

# የአቋም መግለጫ

1 - በሸፍጥና በሴራ፣ ብሎም፣ በክህደት ድንገት በዘር እየፈረጀ፣ ለይቶ የደመሰሰው ወያኔ በአማራው ግዛትም ጭምር ለፈፀመው የአማራን ዘር በአደገኛ: ሁኔታ ፣ ሌሎቹንም የአገራችንን ማኅበረሰብ አባላትን በመጨፍጨፉ በጦር ወንጀለኛነት እና በዘር ማጥፋት ወንጀል ለዓለም ፍ/ቤት እንዲቀርብ አስቸኳይ ዝግጅት እንዲደረግ።

2 - በተለያዩ፣ የሀገራችን ክልሎች ፣ ከኦሮሞ ማህበረሰብ ውጭ የሆኑ አማርኛ ተናጋሪ የአገሪቱን ዜጎች፣ በተለይም የአማራውን ማህበረሰብ በዘር እየለየ የሚመነጥረው ፣ የሚያርደው እና የሚያሳርደው ፣ የሚያፈናቅለው እና ሀብትና ንብረታቸውን የሚያወድመው ኦነግ ( በሌላ ቦታ ግን ለወንጀል አፈፃፀም እንዲያመቸው ሸኔ በሚል የዳቦ ስም የሚጠራው ) የታጠቀው ዘመናዊ መሣሪያ፣ ከኦህዴድ የክልል መንግሥት በምስጢር የሚቸራቸው ሲሆን ፣ በዚህም መሣሪያ፣ የእልፍ አዕላፍትን ንፁሀን ደም እያፈሰሰ በመሆኑ፣ የኦነግ ትጥቅ በአስቸኳይ ተፈትቶ ፣ ወንጀለኛው ቡድን ለሕግ እንዲቀርብ እንዲደረግ ፣ የዜጎቿ መብትና: በሠላም የመኖር: ዋስትና እንዲረጋገጥ።

3 - በአሁኑ ወቅት መንግሥት: ከአሸባሪው ህወሓት ጋር ለመደራደር ቢነሳ ወያኔ ከሽግግር መንግስት ቻርተር (ከ1983 ዓ.ም) በፊት ወደ ነበረበት የትግራይ ምድር: እንዲመለስ እንጠይቃለን::

4 - ለዚህ ሁሉ የእርስ በርስ የዘር እልቂትና ፍጅት ምንጭ የሆነው የህወሓት/ኦነግ የጫካ ፓለቲካ የትግል ሰነድ፣ ወደ መሀል አገር ገብቶ ቀደም : ሲል በቻርተርነት እስከ 1986 ዓ ም ድረስ የቆየውና በኋላም በ1987 ዓ.ም የጎሳ ወይም የቋንቋ ሕገመንግሥት በአስቸኳይ ተወግዶ የዜግነት ፓለቲካን የሚያቀነቅን: ህገመንግስት በምትኩ የሚፀድቅበት አገራዊ ምክክር የሰላምና ብሔራዊ የእርቅ ጉባዔ ፈጥኖ እንዲከናወን አጥብቀን እንጠይቃለን።

5 - በአሁኑ ወቅት ፍትህ ተዛብቶባቸው በግፍ በየወህኒ ቤቱ በሀሰት: ውንጀላ: ተከስሰው በእስር የሚማቅቁ: የባልደራስ አመራሮችን :ጨምሮ የጎሊናና የፓለቲካ እስረኞች፣ ያለአንዳች ቅድመ ሁኔታ በአስቸኳይ እንዲፈቱ ብሎም በአማራው ክልል: ተፈፀመ በተባለው መፈንቅለ መስተዳድር ሰበብ የተገደሉት፣ እነ ጄኔራል አሳምነው ፅጌ፣ ዶክተር አምባቸው መኮንን ፣ እና የእነ ሥዐረ መኮንን ሞት ፣ እንዲሁም የደምቢ ዶሎ ዩኒቨርስቲ ሴት ተማሪዎች ዕገታ ተሰውሮና ተዳፍኖ መቅረት፣ አደገኛ የፍትህ አለመስፈንን ስለሚያመለክት በአፋጣኝ ለህዝባችን ጉዳዩ የት እንደደረሰ ሳይድበሰበስ እንዲገለፅ።

6 - በተለያዩ፣ የሀገራችን ክልሎች ፣ ከኦሮሞ ማህበረሰብ ውጭ የሆኑ የአገሪቱን ዜጎች፣ በተለይም የአማራውን ማህበረሰብ በዘር እየለየ የሚመነጥረው ፣ የሚያርደው እና የሚያሳርደው ፣ የሚያፈናቅለው እና ሀብትና ንብረታቸውን የሚያወድመው ኦነግ ( ሸኔ በሚል የዳቦ ስም የሚጠራው ) የታጠቀው ዘመናዊ መሣሪያ፣ ከኦህዴድ የክልል መንግሥት በምስጢር የሚቸራቸው ሲሆን ፣ በዚህም መሣሪያ፣ የእልፍ አዕላፍትን ንፁሀን ደም እያፈሰሰ በመሆኑ፣ የኦነግ ትጥቅ በአስቸኳይ ተፈትቶ ፣ ወንጀለኛው ቡድን ለሕግ እንዲቀርብ እንዲደረግ ፣ የዜጎቿ መብትና በሠላም የመኖር ዋስትና እንዲረጋገጥ።

7 - በአማራው ክልል በሰበብ አስባቡ ፓለቲካዊ ምክንያቶች የታሠሩ የጦር ባለሙያዎች በአሁኑ ሰዐት ለክልሉ እጅግ አስፈላጊ በመሆናቸው በአስቸኳይ እንዲፈቱ እና አማራው ራሱን በበቂ

ሁኔታ ከወራሪው ኃይል እንዲከላከል፣ በቂ ትጥቅ ና ስንቅ ከበቂ በጀት: ጋር ከማዕከላዊው: መንግስትና: ከክልላዊ አስተዳደሮች እንዲመደብ አበክረን ስንጠይቅ ፣ በጦር አመራሩ ደባ የፈፀሙ : አመራሮች፣ ለፍርድ እንዲቀርቡ በዚህ የአቋም መግለጫችን : በጥብቅ እናሳስባለን።

8 - በዘህ አጋጣሚ ለጊዜው የኢትዮጵያ ውስጣዊ የፓለቲካ መደፍረስ: ባስከተለው: አለመረጋጋት የአገራችን የጎረቤት ጠላት አገሮች: ከምዕራባውያን ሀገሮች ጋር ክንዳቸውን: በማስተባበር: ወያኔን ወደሥልጣን ዳግም ለማምጣት የሚያደርጉትን አዋኪ ሴራና ደባ አጥብቀን እናወግዛለን። እስካሁን ስናደርግ እንደነበረው ሁሉ ለዚህም ተቃውሞአችንን በሁለንተናዊ፣ ሕዝባዊ ቅንብርና ቅንጅት ለሕዝባችን: ለአገራችንና ለዓለም አደባባይ: በፅናት: እና በቆራጥነት: በይፋ እናጋልጣለን። በያለንበት የአዉሮፓ ሃገራት የፖለቲካ መሪዎችን እናናግራለን::
የአዉሮፓ ህብረት ፓርላማ ፣ ኮሚሽንና እያንዳንዱ የአዉሮፓ ሀገራት በኢትዮጵያ ላይ የሚያደርጉትን ጫናና የኢኮኖሚ አቀባ እንዲያነሱ የዲፕሎማሲ ስራዉን እንቀጥላለን::

9 - እንደሚታወቀው በዉጭ የምንገኝ ኢትዮጵያዉያን ሀገራችንን በየጊዜው በተለያዩ መንገዶች እየረዳን ነው:: ወደፊትም እርዳታው በሰፊው እንዲቀጥል መንግስት ኢትዮጵያ ዉስጥ ያለዉን ቢሮክራሲ አስወግዶ በዲያስፖራ የሚገኙ አባላት የእርዳታ እቃዎች ወደ ሀገራችን በቀላሉና በፍጥነት መግባት እንዲችሉ እንዲያደርግ እንጠይቃለን::

## ኢትዮጵያ ከልጆቿ ጋር በሰላም፣ በአንድነት፣ በፍቅር ለዘላለም ትኑር !

ፍራንክፈርት /ጀርመን /

**www.ethiodiaspora.net**